የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፵፬
አዲስ አበባ ሰኔ ፲፫ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም.

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

19th Year No. 44
ADDIS ABABA 20th June 2013

ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፪፻፹፯/፪ሺ፭ ዓ.ም.

የምግብ፣ የመጠጥ እና የፋርማሲዩቲካል ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ..... ...... ገጽ ፮ሺ፰፻፴፮

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፹፯/፪ሺ፭

## የምግብ፣ የመጠጥና የፋርማሲዩቲካል ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩትን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የአስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፩/፪ሺ፫ አንቀጽ ፭ እና አንቀጽ ፴፬ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

፩. **አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የምግብ፣ የመጠጥ እና የፋርማሲዩቲካል ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፹፯/፪ሺ፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. **ትርጓሜ**

በዚህ ደንብ ውስጥ የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር:-

፩/ "ኢንዱስትሪ" እና "የማምረት ሥራ" በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር ፮፻፹፮/፪ሺ፪ አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ (፲፩) እና (፲፪) የተሰጣቸውን ትርጓሜ ይይዛሉ፤

CONTENTS

Regulation No. 287/2013

Food, Beverage and Pharmaceutical Industry Developmen Institute Establishment Council of Ministers Regulation.... ..........................................................Page 6836

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No. 287/2013

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO ESTABLISH FOOD, BEVERAGE AND PHARMACEUT CAL INDUSTRY DEVELOPMENT INSTITUTE

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursu ant to Article 5 and Article 34 of the Definition of Powe and Duties of the Executive Organs of the Federal Democ ratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 691/2010.

1. **Short Title**

This Regulation may be cited as the "Food, Beverag and Pharmaceutical Industry Development Institu Establishment Council of Ministers Regulatio No. 287/2013".

2. **Definition**

In this Regulation unless the context otherwise re quires:

1/ "industry" and "manufacturing activity" sha have the definition provided for under sub article (11) and (12) of Article 2 of the Com mercial Registration and Business Licensin Proclamation No. 686/2010;

፪/ "የምርት ሂደት" ማለት በማምረት ሥራ ክንውን የሚኖር ቅብብሎሽ ነው፤

፫/ "ምግብ" ማለት ማንኛውም በጥሬነቱ በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ የተዘጋጀ በሽያጭ ወይም በሌላ መንገድ ለኅብረተሰቡ ቀርቦ ለሰው ምግብነት የሚውል ነገር ሲሆን፣ የሚታኘክ ማስቲካ፣ ተጨማሪ ምግብ እንዲሁም ምግብ ለማምረት፣ ለማዘጋጀት ወይም ለማከም የሚያገለግል ማንኛውም ንጥረ ነገር የሚያካትት ሆኖ ትምባሆና ለመድኃኒትነት ብቻ የሚያገለግሉ ንጥረ ነገሮችን አይጨምርም፤

፬/ "መጠጥ" ማለት ለሰው መጠጥነት የሚውል ፈሳሽ ነገር ሲሆን የታሸገ ውኃን፣ የፍራፍሬ ጭማቂን፣ ለስላሳ እና የአልኮል መጠጦችን ያካትታል፤

፭/ "የሕክምና መሣሪያ" ማለት የሰውን በሽታ ለመመርመር ወይም ለማከም ጥቅም ላይ የሚውል ማንኛውም መሣሪያ ወይም መገልገያ ሲሆን የተለያዩ የመመርመሪያ፣ የላብራቶሪ፣ የቀዶ ሕክምናና የጥርስ ሕክምና መሣሪያዎችን፣ የቁስል መስፊያ ክሮችን፣ሲሪንጆችን፣ መርፌዎችን፣ ፋሻዎችን፣ ጐዝን፣ ጥጥ፣ ሰው ሠራሽ ጥርሶችን፣ ኬሚካሎችን፣ የጨረር ፊልሞችንና ሌሎች መሰል መሣሪያዎችንና መገልገያዎችን ይጨምራል፤

፮/ "ባሕላዊ መድኃኒት" ማለት የዕፅዋት፣ የእንስሳት ወይም የማዕድን ተዋፅ ሆኖ በነጠላም ሆነ በመቀላቀል ለሰውም ሆነ ለእንስሳት ሕክምና አገልግሎት የሚውል መድኃኒት ነው፤

፯/ "መድኃኒት" ማለት የሰውን በሽታ ለመመርመር፣ ለማከም፣ ለማስታገስ ወይም ለመከላከል የሚያገለግል ማንኛውም ንጥረ ነገር ወይም የንጥረ ነገሮች ውህድ ሲሆን የናርኮቲክና ሣይኮትሮፒክ መድኃኒቶችን፣ ፕሪከርሰር ኬሚካሎችን፣ የባሕል መድኃኒቶችን፣ ደጋፊ ወይም አማራጭ መድኃኒቶችን፣ መርዞችን፣ ደምና የደም ተዋፅዎችን፣ ክትባቶችን ፣ ጨረራ አፍላቂ መድኃኒቶችን፣ ኮስመቲኮችን፣ የሳኒተሪ ዝግጅቶችን እና የሕክምና መሣሪያዎችን ይጨምራል፤

2/ "production process" means sequence of operation in the performance of manufacturing activity;

3/ "food" means any substance semi-processed or processed as raw and supplied to the public for human consumption through sales or otherwise, and includes chewing gum, supplementary food and any substance to be used in the manufacturing, preparation or treatment of food, but does not include tobacco and substances used only as medicine;

4/ "beverage" means any liquid intended for human drinking that includes bottled water, fruit juices, soft drinks, and alcoholic drinks;

5/ "medical instrument" means any instrument or supply that may be used for diagnosis or treatment of a disease in humans, and includes various diagnostic, laboratory, surgery and dental instruments, suturing materials, syringes, needles, bandage, gauze, cotton, artificial teeth, chemicals, x-ray films and other similar instruments and supplies;

6/ "traditional medicine" means any plant, animal or mineral product that can be used independently or in combination for the treatment of human or animal diseases;

7/ "medicine" means any substance or mixture of substances used in the diagnosis, treatment, mitigation or prevention of a disease in human and includes narcotic drugs, psychotropic substances and precursor chemicals, traditional medicines, complementary or alternative medicine; poisons, blood and blood products, vaccine, radioactive pharmaceuticals, cosmetics and sanitary items and medical instruments;

፰/ "ኮስመቲክ" ማለት ሰውነትን ለማጽዳት፣ ለማስዋብ፣ ደም ግባት ለማሣመር ወይም የአካልን ቅርጽና አሠራሩን ሳይቀይር ገጽታን ለመቀየር በገላ ላይ የሚደረግ ማንኛውም ዝግጅት ሲሆን የቆዳ ቅባቶችን፣ ሎሽኖችን፣ ሽቶዎችን፣ የከንፈር ቀለሞችን፣ የጥፍር ቀለምና ማስለቀቂያ፣ የዓይንና የፊት ማስዋቢያ፣ የጸጉር ማቅለሚያዎችን፣ የጠረን መቀየሪያ ዝግጅቶችን፣ ሜዲኬትድ ሳሙናዎችን እና ለእነዚህ ዝግጅቶች መሥሪያ የሚውሉ ንጥረ ነገሮችን ይጨምራል፤

፱/ "የምግብ ኢንዱስትሪ" ማለት ማናቸውንም ምግብ የሚያቀነባብር ወይም የሚያመርት ኢንዱስትሪ ነው፤

፲/ "የመጠጥ ኢንዱስትሪ" ማለት ማናቸውንም መጠጥ የሚያቀነባብር ወይም የሚያመርት ኢንዱስትሪ ነው፤

፲፩/ "ፋርማሲዩቲካል ኢንዱስትሪ" ማለት መድኃኒት፣ ባሕላዊ መድኃኒት፣ ሕክምና መሣሪያ፣ ኮስመቲክ ወይም ከእነዚህ የተወሰኑ ዓይነቶችን አንድ ላይ በማድረግ የሚያመርት ኢንዱስትሪ ነው፤

፲፪/ "ማሸጊያ" ማለት ምግብን፣ መጠጥን ወይም መድኃኒትን በውስጡ ለመሙላት ወይም ለመከተት ወይም ለመጠቅለል የሚያገለግል ማንኛውም መያዣ ሲሆን ከምግቡ፣ ከመጠጡ ወይም ከመድኃኒቱ ጋር ቀጥታ ግንኙነት ያላቸውን መያዣዎችን ወይም ለመጠቅለያ የሚያገለግሉ ሌሎች ዕቃዎችን ይጨምራል፤

፲፫/ "ባዮኢኩቫለንስ ማዕከል" ማለት ሁለት ዓይነት የመድኃኒት ዝግጅቶች በፍቱንነታቸውና ደኅንነታቸው የሚመሳሰሉ መሆናቸው በምርመራ የሚረጋገጥበት ማዕከል ነው፤

፲፬/ "ሚኒስቴር" ማለት የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ነው፤

፲፭/ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው የሴትንም ይጨምራል፡፡

8/ "cosmetic" means any preparation intended to be applied to the human body for cleansing, beautifying the appearance without affecting the body's structure or functions, and includes products such as skin creams, lotions, perfumes, lipsticks, finger-nail polishes, eye and facial make-up preparations, shampoos, permanent waves, hair colors, deodorant, medicated soaps and any ingredient intended for preparing these products;

9/ "food industry" means industry engaged in processing or manufacturing of food;

10/ "beverage industry" means industry engaged in processing or manufacturing of beverage;

11/ "pharmaceutical industry" means industry engaged in manufacturing of medicine, traditional medicine, medical instruments, cosmetics or combination of any of these items;

12/ "packaging material" means any material that may be used for filling, inserting or wrapping or packing food, beverage or medicine, and includes immediate container and other materials for wrapping the product;

13/ "bioequivalence center" means the center in which the similarity of efficacy and safety of two types of medicine products are ascertained by testing;

14/ "Ministry" means the Ministry of Industry;

15/ any expression in the masculine gender includes the feminine.

፫. **መቋቋም**

፩/ የምግብ፣ የመጠጥ እና የፋርማሲዩቲካል ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት (ከዚህ በኋላ "ኢንስቲትዩት"እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የፌደራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

፪/ ኢንስቲትዩቱ ተጠሪነቱ ለሚኒስቴሩ ይሆናል፡፡

፬. **ዋና መሥሪያ ቤት**

የኢንስቲትዩቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ከተማ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በማንኛውም ሥፍራ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ሊኖረው ይችላል፡፡

፭. **ዓላማ**

የኢንስቲትዩቱ ዓላማ ለምግብ፣ ለመጠጥና ለፋርማሲዩቲካል ኢንዱስትሪ ሁለገብ ድጋፍ በመስጠት የቴክኖሎጂ ሽግግር ማፋጠን፣ የልማት እመርታ ማምጣት እና ኢንዱስትሪው በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ማብቃት ይሆናል፡፡

፮. **የኢንስቲትዩቱ ሥልጣንና ተግባር**

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

፩/ የምግብ፣ የመጠጥና ፋርማሲዩቲካል ኢንዱስትሪ ልማትን ለማፋጠን የሚረዱ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችንና መርሐ-ግብሮችን ማዘጋጀትና በመንግሥት ሲፈቀዱም ተግባራዊ ማድረግ፤

፪/ በምግብ፣ በመጠጥና በፋርማሲዩቲካል ኢንዱስትሪ ሊለሙ የሚችሉ ቴክኖሎጂዎችን በምርምርና ስርፀት መለየት፤ በባሕላዊ ምርቶች ላይ እና በአዳዲስ ምርቶች ላይ የምርት ሂደትና የምርት ልማት ሥራ ማከናወንና እነዚህን ቴክኖሎጂዎች ወደ ኢንዱስትሪው በማሸጋገር ወደ ገበያ እንዲገቡ መደገፍ፤ ኢንዱስትሪው የምርምርና ሥርፀት ክፍሎች እንዲያቋቁም መደገፍ፤

3. **Establishment**

1/ The Food, Beverage and Pharmaceutical Industry Development Institute (hereinafter the "Institute") is hereby established as an autonomous federal government institution having its own legal personality.

2/ The Institute shall be accountable to the Ministry.

4. **Head Office**

The Institute shall have its head office in Addis Ababa and may have branch offices elsewhere, as may be necessary.

5. **Objective**

The objective of the Institute shall be to provide all-round support to the food, beverage and pharmaceutical industry and thereby accelerate technology transfer, achieve transformation and enable the industry to be competitive at international level.

6. **Powers and Duties of the Institute**

The Institute shall have the powers and duties to:

1/ formulate policies, strategies and action plans that assist in the acceleration of the development of food, beverage and pharmaceutical industry, and implement the same upon approval by the government;

2/ identify through research and development relevant technologies applicable to the development of the food, beverage and pharmaceutical industry; perform production process and product development activities on new and traditional products and transfer these technologies to the industry and support them to enter the market; and assist the industry to establish research and development units;

፫/ የምግብ፣ የመጠጥና ፋርማሲዩቲካል ኢንዱስትሪ ለማሳደግ የሚያግዙ የገበያ ጥናትን ጨምሮ ሌሎች የጥናትና የምርምር ሥራዎችን ማከናወን፤ የኢንዱስትሪ ምርቶች በአገር ውስጥ እንዲሁም በዓለም ገበያ ለማስተዋወቅ ድጋፍ መስጠት፤ ውጤታማ የግብይት ሥርዓት እንዲዘረጋ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት መሥራት፤

፬/ ለምግብ፣ መጠጥና ፋርማሲዩቲካል ኢንዱስትሪ ልማት አስፈላጊ የሆኑ የቴክኖሎጂ፣ የገበያ እና ሌሎች መረጃዎችን መሰብሰብ፣ መተንተን፣ ማደራጀት እና እንደ አስፈላጊነቱ ለተጠቃሚዎች ማሰራጨት፤

፭/ የምግብ፣ የመጠጥና ፋርማሲዩቲካል ኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት የሚያስችሉ የፕሮጀክት ፕሮፋሎችን ማዘጋጀትና ማሠራጨት፤ በፕሮጀክት አፈጻጸም ላይ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ እንዲሁም በአፈፃፀም ላይ ለሚከሰቱት ችግሮች መፍትሔ መስጠት፤ የኢንቨስትመንት ማነቆዎች እንዲወገዱ ድጋፍ መስጠትና ፕሮሞሽን ማካሄድ፤

፮/ በምግብ፣ መጠጥና ፋርማሲዩቲካል ኢንዱስትሪ ልማት ዘርፍ ለሚሠማሩ ባለሀብቶች በቴክኖሎጂ መረጣ፣ በድርድር፣ በግንባታ፣ በተከላ እና በሙከራ ምርት የምክር ድጋፍ መስጠት፤

፯/ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር፣ የምግብ፣ የመጠጥና ፋርማሲዩቲካል ኢንዱስትሪ ዘርፍ ልማትን የሚያግዙና ተወዳዳሪ የሚያደርጉ የቴክኖሎጂ፣ የቴክኒክ፣ የግብይት፣ የሥራ አመራር እና ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ተግባር ተኮር ሥልጠናዎችን ማዘጋጀትና መስጠት፤



3/ conduct other study and research activities including market research that support the development of the food, beverage and pharmaceutical industry; assist industry to promote their products in the domestic as well as international markets; and work closely with relevant stakeholders in order to implement effective marketing systems in the industry;

4/ collect, analyze and organize technological, market and other data necessary for the development of the food, beverage and pharmaceutical industry and disseminate same to users, as may be necessary;

5/ prepare and disseminate project profiles that may help expansion of investment in the food, beverage and pharmaceutical industry; follow up and assist project implementation and provide remedies for problems encountered during implementation, assist the industry in getting rid of investment bottlenecks and conduct promotional activities;

6/ assist investors desiring to engage in the food, beverage and pharmaceutical industry by providing advise in the selection of technology, negotiation, construction, erection and commissioning;

7/ in collaboration with other stake holders, prepare and conduct practical trainings on technology, technical matters, marketing and management and other tailor-made trainings that may assist the development and competitiveness of the food, beverage and pharmaceutical industry;

፰/ ለምግብ፣ መጠጥና ፋርማሲዩቲካል ኢንዱስትሪ በምርት ሂደት፣ በምርት ዕቅድና በጥራት ቁጥጥር ላይ ድጋፍና የማማከር አገልግሎት መስጠት፤ የናሙና ምርት ማምረቻና ላብራቶሪዎች በማቋቋም መደገፍ፣ ለሚያመርቷቸው ምርቶች ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ የፍተሻ አገልግሎት መስጠት፣ ኢንዱስትሪው የፍተሻ ላብራቶሪዎች እንዲያቋቁም ማበረታታትና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የሚያስችላቸውን ሠርተፊኬሽን እንዲያገኙ ማስቻል፤

፱/ በዓለም አቀፍ ደረጃ ብቃትን ጠብቆ ኢንዱስትሪውን ለመደገፍ እንዲችል በቁርኝት መርሐ ግብር አቅሙን መገንባት፤ ተመሣሣይ ዓላማ ካላቸው በአገር ውስጥ እና በውጭ አገር ከሚገኙ የግልና የመንግሥት ተቋማት ጋር ትብብር ማድረግ እና በግል ተቋማት መካከልም ተመሣሣይ ትብብር እንዲደረግ ማበረታታት፤

፲/ ከዩኒቨርሲቲዎች ጋር የምርትና የሰው ኃይል ልማትን በተመለከተ በመተባበር መሥራትና በጋራ የምርምር ሥራዎችን ማካሄድ፤ ኢንዱስትሪው ከዩኒቨርሲቲዎች ጋር ትስስር እንዲኖረው ማገዝ፤ የኢንዱስትሪውን የዝቅተኛና መካከለኛ የሰው ኃይል ፍላጎት ለማሟላት ከቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ተቋማት ጋር በቅንጅት መሥራት፤

፲፩/ የምግብ፣ የመጠጥና የፋርማሲዩቲካል ኢንዱስትሪ ልማትን ሊያፋጥኑና ተወዳዳሪ ሊያደርጉ የሚችሉ የዓለም አቀፍ የምርጥ ተሞክሮዎች ጥናት ማካሄድና የሚቀመሩትን ተሞክሮዎች ተግባራዊ ለማድረግ ለኢንዱስትሪው ድጋፍ መስጠት፤

፲፪/ ለዘርፉ የግብዓቶች አቅርቦት በዓይነት፣ በመጠንና በጥራት አስተማማኝ እንዲሆን የግብዓት ኢንዱስትሪው እንዲለማ መደገፍ፤ ከጥሬ ዕቃ አመራረት እስከ ዓለም አቀፍ ገበያ

8/ provide consultancy services to food, beverage and pharmaceutical industry concerning production process, production planning and quality assurance; establish pilot plants and laboratories to support the industry, provide international-level testing services; encourage industry to establish laboratories and assist them to get certification so as to make them internationally competitive;

9/ build its capacity to international standard through twinning programs so as to support the industry effectively; cooperate with local and foreign governmental and private institutions having similar objectives and also encourage similar co-operation between private institutions;

10/ work in collaboration with universities in product and human resource development, conduct joint research activities, assist the industry in establishing linkages with the universities; work with technical and vocational training centers to build the human resource of the industry at lower and middle levels;

11/ undertake international benchmarking studies to enhance the development and competitiveness of the food, beverage and pharmaceutical industry and facilitate the implementation of compiled best practices by the industry;

12/ support the development of input industry so as to ensure the regular availability of inputs to the industry in terms of variety, quantity and quality; extend the necessary support and

ድረስ በምርቶች እሴት ሰንሰለት መሠረት በዘርፉ ተዋናዮች መካከል ያለው ትስስር ውጤታማ እንዲሆን አስፈላጊውን ድጋፍና ክትትል ማድረግ፤ በተለይም በዘርፉ የተሠማሩ የጥቃቅንና አነስተኛ አምራች ኢንዱስትሪው ከመካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪው ጋር ውጤታማ የምርት፣ የቴክኖሎጂና የሥልጠና ትስስር እንዲኖረው መደገፍ፤

፲፫/ የአገር ውስጥና የውጪ ባለሀብቶች በዘርፉ ላይ ለመሠማራት እንዲነሳሱ የምግብ፣ የመጠጥና የፋርማሲዩቲካል ኢንዱስትሪ ቀጠናዎች እንዲለሙ ማበረታታት፤ በኢንዱስትሪ ቀጠናዎች ውስጥ የሚሠሩ ባለሃብቶችን መደገፍ፤

፲፬/ በዘርፉ አዳዲስና ተወዳዳሪ ባለሀብቶችን ለመፍጠር የኢንተርፕረነርሽፕ ልማት ፕሮግራም መዘርጋትና የኢንኩቤሽን ማዕከላትን ማቋቋም፤

፲፭/ የምግብ፣ የመጠጥና የፋርማሲዩቲካል ኢንዱስትሪው በገበያ ተወዳዳሪ እንዲሆን የማሸጊያ ምርቶች ኢንዱስትሪ ልማትን መደገፍ፤

፲፮/ በዘርፉ ተዋናዮች የሚገኙ የምርምርና የቴክኖሎጂ ውጤቶች የአዕምሯዊ ንብረት ባለቤትነት መብት እንዲጠበቅላቸው ድጋፍ መስጠት፤

፲፯/ የምግብ፣ የመጠጥ እና የፋርማሲዩቲካል ኢንዱስትሪ ታዳሽ የኃይል ምንጮችን እንዲጠቀም እና የአካባቢ ብክለት እንዳያስከትል ድጋፍ መስጠት፤

፲፰/ የባዮ-ኢኩቫለንስ ማዕከል በማጠናከር በኢትዮጵያ ያሉት የፋርማሲዩቲካል ኢንዱስትሪዎች ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ከማዕከሉ ድጋፍ እንዲያገኙ ማድረግ፤

follow up to ensure effective linkage among the actors of the sector based on the respective value chains starting from raw material up to global market; and also support the linkage of micro and small manufacturing enterprises with medium and large industry in terms of production, processing technology and training;

13/ encourage the development of food, beverage and pharmaceutical industry zones to mobilize national and foreign investors to the sector, and support investors operating in the industry zones;

14/ establish entrepreneurship development program and incubation centers to create new and vibrant entrepreneurs in the sector;

15/ support the development of packaging industry to make food, beverage and pharmaceutical industry competitive in the market;

16/ provide support in the acquisition of intellectual property rights and patents for research and technology outputs developed by the sector actors;

17/ provide support to food, beverage and pharmaceutical industry to use renewable energy sources and to operate in an environment friendly manner;

18/ strengthen the bio-equivalence center so that it provides the requisite services to pharmaceutical industry so as to make them competitive;

፲፱/ በድኅረ-ምርት የሚያጋጥሙ የምርት ብክነቶችን ለመቀነስ ድኅረ-ምርት ቴክኖሎጂዎች፣ የማቀዝቀዣ ሰንሰለቶች፣ ዘመናዊ መጋዘኖች፣ ዘመናዊ ትራንስፖርት እና ሌሎች አስፈላጊ የሎጂስቲክስ መሠረተ-ልማቶች እንዲስፋፉ መደገፍ፤

፳/ የምግብ፣ የመጠጥ እና የፋርማሲዩቲካል ኢንዱስትሪ ማኅበራት ለዘርፉ ንግድና ኢንቨስትመንት ዕድገት የሚጠበቅባቸውን ሚና እንዲጫወቱ የአቅም ግንባታ ድጋፎች መስጠት፤

፳፩/ ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች በመንግሥት በሚወሰን ተመን መሠረት የአገልግሎት ዋጋ የማስከፈል፤

፳፪/ የንብረት ባለቤት መሆን፤ ውል መዋዋል፤ በራሱ ስም መክሰስና መከሰስ፤

፳፫/ ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ማከናወን፡፡

፯. <u>**የኢንስቲትዩቱ አቋም**</u>

ኢንስቲትዩቱ:-

፩/ የአማካሪ ምክር ቤት (ከዚህ በኋላ "ምክር ቤት" እየተባለ የሚጠራ)፤

፪/ በመንግሥት የሚሾሙ አንድ ዋና ዳይሬክተር እና እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፤ እና

፫/ አስፈላጊው ሠራተኞች፤

ይኖሩታል፡፡

፰. <u>**የምክር ቤቱ አባላት**</u>

፩/ የምክር ቤቱ ሰብሳቢና አባላት አግባብነት ካላቸው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና ከግሉ ዘርፍ የተውጣጡ ሆነው በመንግሥት ይሰየማሉ፡፡



19/ promote post-harvest technologies, cold chain, modern ware houses, modern transport facilities and other necessary logistics for the sector to reduce post-harvest losses;

20/ provide capacity building support to the food, beverage and pharmaceutical industry associations so that they can play their proper role in the promotion of trade and investment in the sector;

21/ charge fees for the services it renders in accordance with the rate approved by the government;

22/ own property, enter into contracts, sue and be sued in its own name;

23/ perform other related activities necessary for the attainment of its objective.

7. <u>**Organization of the Institute**</u>

The Institute shall have:

1/ an Advisory Council (hereinafter the "Council");

2/ a Director General and, as may be necessary, Deputy Director Generals to be appointed by the government; and

3/ the necessary staff.

8. <u>**Members of the Advisory Council**</u>

1/ The Chairperson and members of the Council shall be drawn from the appropriate government offices and the private sector and be assigned by the government.

፪/ የምክር ቤቱ አባላት ቁጥር እንደአስፈላጊነቱ ይወሰናል፡፡

2/ The number of members of the Council shall be determined as required.

፱. የምክር ቤቱ ተግባራት

ምክር ቤቱ:-

፩/ ኢንስቲትዩቱ በሚያከናውናቸው ተግባራት ላይ ያማክራል፤

፪/ የምግብ፣ የመጠጥና የፋርማሲዩቲካል ኢንዱስትሪ ልማትን ለማፋጠን የተዘጋጁ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችን፣ ዕቅዶችን፣ ጥናቶችን እና ምርምሮችን ይገመግማል፤ አስተያየቱንም ይሰጣል፤

፫/ በአቅም ግንባታ መርሐ-ግብሮች ላይ አስተያየት ይሰጣል፤

፬/ የኢንስቲትዩቱን የዕቅድ አፈፃፀም በየሦስት ወሩ እየገመገመ የመፍትሔ አቅጣጫ ያስቀምጣል፡፡

9. Duties of the Council

The Council shall:

1/ advise the Institute on its activities;

2/ evaluate and forward its recommendation on polices, strategies, plans, studies and research formulated with a view to accelerating the development of the food, beverage and pharmaceutical industry;

3/ forward its opinions on capacity building programs;

4/ evaluate the implementation of the plans of the Institute every three months and suggest remedial directions.

፲. የምክር ቤቱ ስብሰባዎች

፩/ ምክር ቤቱ በየሶስት ወሩ ይሰበሰባል፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማናቸውም ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል፡፡

፪/ ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በስብሰባ ላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፡፡

10. Meetings of the Council

1/ The Council shall meet every three months; provided, however, that it may meet at any time where necessary.

2/ There shall be quorum where more than half of the members of the Council are present at a meeting.

፲፩. የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር

፩/ ዋና ዳይሬክተሩ የኢንስቲትዩቱ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሆኖ የኢንስቲትዩቱን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል፡፡

11. Powers and Duties of the Director General

1/ The Director General shall be the chief executive officer of the Institute and shall direct and administer the activities of the Institute.

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፦

ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፮ የተመለከቱትን የኢንስቲትዩቱን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤

ለ) የኢንስቲትዩቱን ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች በፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎች መሠረት እንዲሁም የኢንስቲትዩቱን ዓላማ በማስፈጸም ሥራ ላይ የሚሠማሩ ባለሙያዎችን የፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎችን መሠረታዊ መርሆዎች ተከትሎ በመንግሥት በሚጸድቅ መመሪያ መሠረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤

ሐ) የኢንስቲትዩቱን ስትራቴጂክ ዕቅድ፣ ዓመታዊ ዕቅድ፣ የሥራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፤ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤

መ) ለኢንስቲትዩቱ በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

ሠ) ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ኢንስቲትዩቱን ይወክላል፤

ረ) የኢንስቲትዩቱን የሥራ አፈጻጸምና የሂሳብ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል።

፫/ ዋና ዳይሬክተሩ ለኢንስቲትዩቱ ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለኢንስቲትዩቱ ሌሎች ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል።

2/ Without limiting the generality of sub-article (1) of this Article, the Director General shall:

a) exercise the powers and duties of the Institute specified under Article 6 of this Regulation;

b) employ and administer employees engaged in support services of the Institute in accordance with the federal civil service laws and, in the case of professionals engaged in the core functions of the Institute, in accordance with directives approved by the government following the basic principles of the federal civil service laws;

c) prepare and submit to the Ministry the strategic plans, annual plans, work programs and budgets of the Institute and implement same upon approval;

d) effect payments in accordance with the approved budget and work program of the Institute;

e) represent the Institute in its dealings with third parties;

f) prepare and submit to the Ministry the performance and financial reports of the Institute.

3/ The Director General may delegate part of his powers and duties to other officers and staff of the Institute to the extent necessary for the effective performance of the activities of the Institute.

፲፪. **በጀት**

የኢንስቲትዩቱ በጀት በመንግሥት ይመደባል፡፡

፲፫. **የሂሣብ መዛግብት**

፩/ ኢንስቲትዩቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል፡፡

፪/ የኢንስቲትዩቱ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ፡፡

፲፬. **ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ሰኔ ፲፫ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም

ኃይለማርያም ደሳለኝ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ

12. **Budget**

The budget of the Institute shall be allocated by the government.

13. **Book of Accounts**

1/ The Institute shall keep complete and accurate books of accounts.

2/ The books of accounts and financial documents of the Institute shall be audited annually by the Auditor General or an auditor assigned by him.

14. **Effective Date**

This Regulation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

Done at Addis Ababa, this 20th day of June, 2013.

HAILEMARIAM DESSALEGN

PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA